# አማራ አማን ነወይ! በላይነህ አባተ



አማን ነወይ ሸዋ፣ አጣዬ አማን ነወይ፤
ካድራ ወንዝ መተክል፣ ወሎስ አማን ነወይ?
የእነ ስበር አገር ሲነድ አየነው ወይ?

አማን ነወይ ህዝቡ፣ አማራ ተዳር ዳር፤
ስንት ሌሊት ያንጋ፣ ይሄ ችሎ ማደር?

አማን ነወይ ደሴ፣ አማን ነወይ ምንጃር፤
አማን ነወይ ማርቆስ፣ አማን ነወይ ጎንደር፤
አማን ነወይ ታቦር፣ ወልድያ ባህርዳር፤
ምናለ ሲታረድ፣ ወገኑ ተዳር ዳር?

አርማጮ አማን ነወይ፣ ጃናሞራ ሰሜን፤
ሸበል አማን ነወይ፣ ጉባያና ለምጨን፤
ወልድያ አማን ነወይ፣ ቦረና ሳይንትን፤
መራኛ አማን ነውይ፣ አንኮበር ጥግ ጥጉን፤
ወዴት ልንደርስ ነው፣ ተገፍተን ተገፍተን?

ጠለምት አማን ነወይ፣ ራያ ወልቃይት፤
ደራስ አማን ነወይ፣ ከሚሴ መተከል፤
ዘር የሚዘሩበት፣ ነቅለው የኛን ተክል!

ደንበያ አማን ነወይ፣ አማን ነወይ ዳሞት፡
ሰቆጣ አማን ነወይ፣ አማን ነወይ ጋይንት፤
ብቸና አማን ነወይ፣ አማን ነወይ ሰቀልት፤
ባቲስ አማን ነወይ፣ አማን ነወይ ተጉለት፤
ታልጋው አስወርደው፣ ወለል ቁጢ በል ያሉት?

አማን ነወይ ዳባት፣ ጃግኒስ አማን ነወይ፤
አማን ነወይ መቄት፣ ሽንኮራ አማን ነወይ፤
አማን ነወይ ሞጣ፣ እስቴስ አማን ነወይ፤
አቸፈር ወንድዬ፣ ማጄቴ አማን ነወይ፤
መቻል ብሎ ማደር፣ ጤና ላይሆን ነወይ?

አማን ነወይ ግሼ፣ ሰቆጣ አማን ነወይ፤
አማን ነወይ ፋርጣ፣ ዳንግላ አማን ነወይ፤
እነሴ እነብሴ፣ በለሳ አማን ነወይ፤
አማን ነወይ ዋድላ፣ ጭልጋስ አማን ነወይ፤
በደል ቁና ሞልቶ፣ ተርፎ አልፈሰሰም ወይ?

አማን ነወይ ዳሽን፣ ጮጩስ አማን ነወይ፤
በላያ ተራራ፣ የጎፍ አማን ነወይ፤
ቆሞ መመልከቱ፣ አልሰለቸውም ወይ?

አማን ነወይ ዓባይ፣ ግዮን የኦሪቱ፤
ተከዜ አማን ነወይ፣ ስንቱን ያየው ባይኑ፤
አማን ነወይ ጀማ፣ መሀሉ ዳርዳሩ፤
አማን ነወይ በሽሎ፣ ድንብልዙና ስርጡ፤
አልሰለቸውም ወይ፣ ዝምብሎ መፍሰሱ?

ጦቢያስ አማን ናት ወይ፣ ተዘጋጅቷል ሕዝቡ፣
ምስር ፈረስ ሆና፣ ሲመጣ ግራኙ፡፡

አማን ነወይ መንደር፣ ቅዬውና አድባሩ፤
አማራ አማን ነወይ፣ ጤናውና ክብሩ፤
አላስቆጣውም ወይ፣ ዛሬም መታረዱ?
በአጥንቱ ካስማነት፣ ባቆማት አገሩ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መጀመርያ ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.

እንደገና ሚያዚያ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.

The Ignored Amara Genocide: https://welkait.com/wp-content/uploads/2018/04/AMARA-GENOCIDE-IN-ETHIOPIA-from-1991-%E2%80%93-2015-STUDY-MORESH-WEGENIE-AMARA-ORGANIZATION.pdf